ለምን ሰላሚኝ፡ ምን መሰላችሁ ... ለመኖር ስል፣ ሰው ለመሆን ስል፣ በሕይወት ለመኖር ስል. ለመሥዋም ስል፣ ወደፊት ለመወርወር ስል ... ብዙ ነገሮችን በጅነት አሳተባለሁ። ጌታዬ አላህ ጅነት ያስገባኝ አያስገባኝ የማላውቅ ብሆንም ግና በርካታ ጉዳዮቼን ጂንነት ነኝ አቆራኝለሁ። የሰለት ተሰለት ሕይወቴን ጭምር ከጅነት ጋር አስተሳስሬአለሁ። ለምሳሌ. በጠራራው ፀሐይ ከባድ ዕቃ ተሸክሜ ስሄድ ከደከመኝ አረፍ ብዬ አንሻአላህ ነልፋፋል ሊየልኩ ጅነትን አስባለሁ። ታከሲ ለመጠበቅ ረጅም ሰዓት እኛ አስከንጉጠጉ ድረስ ቆሜ ከደከመኝ በጅነት አርፋለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለ ሩንያ ላይ ድካሜ፣ ሀመሜ፣ ጠባጠረዲ፣ አንግልቴ፣ ሁሉ አስብ አስብና አንዴት ልርሳው ስል ጅንትን ፈትለፈቴ አመላለሁ። ጌታዬ ሁኔታዬን ሁሉ ታያለህ ድካሜን፣ ላቤን፣ ጫነሳት መጮ ቆሬን፣ መገርጣቴን ሁሉ በጅነት ካሰኝ ብዬ አለምናለሁ፤ ጌታዬን አማፅናለሁ።

አም ጅንትን አልማለሁ ... ጉልበት ለማግኘት፣ ለመበርታት፣ ለመጠንከር ስል በድካሜ ላይ በሀላብ ጅንትን አነነጫለሁ፣ በቁስሌ ላይ ጅንትን አፈሳለሁ። ያኔ አበረታለሁ። በመከራዬና ፈተናዬ ጪለጥ ሁሉ ጅነት ለኔ ቅርብ ናት። ሰው ቢበድለኝ፣ ያላግባብ ቢዘልፈኝ፣ ከብሬን ቢዲየርድ፣ አሳንሶ ቢመለከተኝ፣ ቢንቀኝ፣ ሥሜን ቢያጠፋ፣ ቢሰርቀኝ፣ ቢገፋኝ ... አይዞኝ ሙሐመዱ በጅነት ትካሳለህ ብዬ አኔን አጽናናለሁ፤ ራሴን አበረታ ታዋለሁ።

ጅንትማ በምናብ ዮቮግር ጊዜ ደራሼ ናት። በድካም ወቅት ተስፋዬ ናት። ጅነት በበሽታዬ መድኃኒቴ፣ ጅነት በዝለቴ ኪኒኒዬ ናት። ጅነትን ሳስብ ድካሜ ሁሉ ብን ብሎ ያጠፋል፤ ጅንትን ተስፋ ሳደርግ ችግሬን ሁሉ አረሳለሁ። ሕመሜን በሙሉ አዘነጋሪሁ። መታገስ በማልጎለው ነገር ላይ ጭምር ጥርሴን ነክሼ አታገሣለሁ። ውዳጆ፣ ጅነትን ማሰብ ዱንያ ላይ ለሚገጥሙን በርካታ ፈተናዎች መድኃኒት ነው። ለብዙ አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ህመሞች ፈውስ ነው። ለብዙ ቁስሎችም ሕክምና ነው። የአላህ መልዕክተኛ ሶ.ዐ.ወ. ባመክ ሰዎች ከባድ ማሰቃየት ለደረሰባቸው ለያሲር ቤተሰብ ምንም ሊያደርጉላቸው ባለመቻላቸው በጅነት ነበር ያጽናኗቸው "የያሲር ቤተሰብ ሆይ ታገሱ፤ ቀጠሮአችሁ ጀነት ነው።" ነበር ያሏቸው። እነ ቢላል ጅነትን አያስቡ በኡመያ የግርፋት ቅጣት ላይ ,ታግሰዋል። ሰሚራ የተባለች ጥቁር ሴት ጅነትን አስባ ከሚጥላት በሽታ አለመዳንን መርጣለች። ጅነትን ያሰቡ ደጋግ ሶሐቦች ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በበድር ዘመቻ ላይ የጠላትን የተደራጀ ጦር አልፈሩም።

ጀነትን ያሰበ ምኒሰኮች በአሐዱ ዘመቻ ላይ ደስተኛ ሆነው ተራ በተራ ነበር ሰግኑት ሆነው ነወደቱት። ጀነትን ያሰበ በተበተከ ዘመቻ ሐሩር ቁሩ አልበገራቸዉም።

ጀነት የምትናፈቅ ሽልማት ናት። ጀነት የተበዳይ መካሻ አገር ናት። ተወዳጁ ጀዕፈር በሙኢታ ዘመቻ ያጡትን ኢጆች በጀነት ዉስጥ ከንፎች ይካሳሉ፤ የሰፅድ መሀረብ በጀነት ዉስጥ ከየትኛዉም የዱንያ ላይ ሐር በላይ ትለሰልሳለች፣ ሐሰንና ሑሴን የጀነት ውጣት የሆኑት በምክንያት ነው፣ ከሐራም ራሱን አርቆ በአላህ ዒባዳ ያደገ ወጣት ጀነት ቃል የተገባለት በመታገሱ ነው።

ወዳጆቼ ... ዱንያ ላይ እንግልታችሁ ሲበዛ ጀነትን አስቡ፣ በበሽታ ወድቃችሁ ስትሰነብቱ ጀነትን አስቡ፣ መከራ ሲደራረብባችሁ ጀነትን አስቡ፣ ስትበደሉ ጀነትን አስቡ፣ ሐዘን ሲወርሣችሁ ጀነትን አስቡ፣ ስትንገላቱ ጀነትን አስቡ፣ ሸክማችሁ ሲበዛ ጀነትን አስቡ፣ በዱንያ ድካሞች ላይ ሁሉ ጀነትን አስቡ፣ አሻግራችሁ ጀነትን እዩ። ጀነትን ስታስቡ ችግራችሁ ይከስማል፣ ህመማችሁ ይቀልላል፣ መከራችሁ ይወገዳል፣ ድካማችሁ ይጠፋል፣ ሸክማችሁ ገለባ ይሆናል፣ ሐዘናችሁ ይረሳል፣ ጉዳታችሁ ያንሳል። ጀነትን አስቡና ኢንሻአላህ ነገ እናርፋለን በሉና ታገሱ፤ ኢንሻአላህ ነገ እንካሳለን በሉና አላህ የወደደላችሁን ዉደዱ፣ ኢንሻአላህ ነገ እንደሠታለን በሉና በሐዘናችሁ ተጽናኑ።

ጀነትን ስናስብ ጀነት ዉስጥ አብዝተን የምንናፍቃቸው ረሱላችን አሉ፤ ምርጦቹ የአላህ ነቢያት አሉ፣ የምንወዳቸው ሶሐቦች አሉ፣ ደጋግ የአላህ ባሮች አሉ፣ ዱንያ ላይ ልናገኛቸው ተመኝተን ሳናገኛቸው ወደ አኺራ የቀደሙ ተናፋቂዎች ሁሉ አሉ። ጀነት ዉስጥ ዐይን ያላየው፣ ጆሮ ያልሰማው፣ በልብ ላይ ዉልብ ብሎ የማያውቅ ፀጋ የተባለ ሁሉ አለ። ጀነት ዉስጥ ዱንያ ላይ ስንወደው የነበረ ነገር ሁሉ አለ፣ ዕረፍትና መዝናናት አለ። ለዚህ ሁሉ ስንል ጀነትን እናስባለን። ጀነትን ስናስብም የዛሬ መከራችንን ሁሉ እንረሳለን። ጀነት የብርታት መርፌያችን ናት። ጀነት ጉልበታችን ናት። ወዳጆቼ! የዱንያን ላይ ችግሮች አትፍሩ፣ መከራ እንግልቶቿንም አትፍሩ። ሁሉም በጎ ፍሬ አላቸዉና አትደናገጡ።

ወዳጆቼ ... ጀነት ዱንያ ላይ ያሳለፍነዉን መከራና ችግር ሁሉ ወዲያው እዚያ እንደገባን በቅጽበት የምንረሳበት ሁሉ ሞልቶ የተትረፈረፈበት የድሎት አገር ነው። በርግጥ ብዙ ነገሮች ጉዳታችን ሁሉ አጠቃለው የመካስ ጉልበት የላቸዉም። ጀነት ግን ከመጠን በላይ የምንካስበት አገር ነው። የሙአሚን ዕረፍቱ ጀነት ነው። አላህ ሆይ ጀነትህን ስጠን።

አላህ ያለ ቀን

ጓዳኞቹ ... ብዙዎች ሲበረቱና ሌሎችንም ሲያበረቱ "ኢንሻአላህ አላህ ያለ ቀን" ሰሉ ትነግላችሁ ሊይደል...!! አዎ በምድር ላይ አላህ ያለው ነገር አንጂ የሚሆን ምንም ነገር የለም:: አላህ ያለው ነገር አላህ ባለው ቀንና ጊዜ ይሆናል፤ አላህ ያላለው ግን ፈጽሞ ሊሆን ሊችልም:: ለዚህም ነው እኛ ሙስሊሞች ነገሮችን ከአላህ ጋር የምናስተሳስረው:: በንግግሮቻችን ዉስጥ ሁሉ "ኢንሻአላህ አላህ፤ ያለ ቀን" የምንለው: : ከራሃችን ጥረት በላይ የአላህን ቀንና ቀጠሮ እንጠብቃለን::

እናም ወዳጄ ከቀንህም በላይ የአላህን ቀን በርግጠኝነት ጠብቅ፣ የአላህን ቃልን ቀጠሮ በፅኑ እመን፣ በአላህ ቃልኪዳን ፍፁም በሆነ መልኩ ተማመን:: በሥራህ፣ በኑሮህ፣ በሀሳብህ፣ በእምነትህ፣ በተስፋህ ... እየተጋህ የአላህ ቀን ጠብቅ::

አዎ አላህ ቀን አለው:: አላህ ጊዜ አለው::አላህ ቀጠሮ አለው:: አላህ ፈቃድ አለው:: አላህ ዉሳኔ አለው:: በአላህ ፈቃድ፣ አላህ ባለው ቀን ... ብለህ የማታሳካው ምንም ምንም ነገር አይኖርም ኢንሻአላህ::

አትፍራ በአላህ ተማመን:: አትስጋ በፈጣሪህ እመን:: ብዙ ነገሮችን መቼ ይሆን የሚሆኑት እያልክ አትብሰልሰል፣ ብዙ አትባክን በሀሳብም አትሸርሸር፣ አትድከም በሐዘንም አትለቅ:: ሁሌም አላህን ጠብቅ:: አላህን ስትጠብቅ አታጣዉም ፈትለፈትህ ታገኘዋለህ::

እና አልኩህ .. አላህ ያለ ቀን አላህ ያለው ነገር ይሆናል፤ እሱ የሻዉን በሻው ቀን ይፈፀማል፣ እሱ የፈቀደዉን በፈቀደው ጊዜ ያደርጋል፣ እሱ የፈረደዉን በፈለገው ጊዜ ያፀናል::

ከነገራት ወደፈት በመቅድም በሀሳብም በጉልበትም ብዙ አትባክን:: አላህ ያለ ቀን ትምህርትህን ትጨርሳለህ፣ አላህ ያለ ቀን ሥራ ታገኛለህ፣ አላህ ያለ ቀን ታገባለህ፣ አላህ ያለ ቀን ልጅ ታገኛለህ፣ አላህ ያለ ቀን ወደ አገርህ ትገባለህ፣ አላህ ያለ ቀን ትድናለህ፣ አላህ ያለ ቀን ... ግና ሰበቡን አታድርስ አልልህም። በደንብ ተፍጨርጭር።

ይህ መጽሐፍ ከተዘጋጀ ቆየ:: አላህ ባለው ቀን ያልቃል ተብሎ የተጀመረ ነበር:: በርግጥም አላህ ባለው ቀን ታተመ:: አላህ ባለው ቀንም እጅህ/ እጅሽ ገባ:: **በርግጥም አላህ ቀን አለው::** ሶባሐል ኸይር!

ከትላልቅ ጂሃዶች መካከል

ወዳጆቼ ... ከትላልቅ ትግሎች መካከል አንዱ የትኛው መሠላችሁ:: ሐዘንን መታገሏ ነው:: ሐዘን ስላችሁ የትኛው መሠላችሁ:: በቅርብ ሰው ሞት ምክንያት የሚደርስብንን ሐዘንም ሊሆን ይችላል:: እጅግ የምንወደውን ሰው በምናጣበት ጊዜ የሚደረስብን ሊሆን ይችላል:: አሥ ይሄ በርግጥም ይህ ትልቁ ሐዘን ነው:: ግና ዱንያ ሐዘኗ ብዙ ነው:: መድከም ሐዘንን ያመጣል:: ስኬት ማጣት፣ ኪሣራ፣ ችግር፣ መውደቅ፣ ጥሩ ስሜት አለመሆን ጭምር ሐዘንና ትካዜን ያስከትላል:: ቅሰም ይሰብራል፣ ሞራል ይነካል፣ አንገት ያስደፋል:: ዱንያ ላይ አሉታዊ ስሜት የሚያመጡብን ነገሮች ሁሉ የደስታ ተቃራኒ የሆነው ሐዘን ናቸው:: እነኚህ ስሜቶችና ከስተቶች በሕይወት እስካለን ድረስም የሚቋረጡ አይደሉም:: እነኚህን ሁሉ መታገል ከመውደቅ ወደ መነሳት፣ ከኪሣራ ወደ ትርፍ፣ ከችግር ወደ ድሎት፣ ከመጥፎ ስሜት ወደ ጥሩ ስሜት ለመምጣት የሚደረገው ትግል ራሱን የቻለ ትልቅ ትግል ነው:: ካልታገልን እንወድቃለን፣ እንሠበራለን፣ ከሰረን እንቀራለን፣ እንጠፋለን::

ደስ የሚለው ነገር በነኚህ በሚደርሱብን የዱንያ ላይ መከራዎችና ሐዘኖች ምንዳ የምናገኝ መሆኑ ነው:: የሚያገኘንና የሚነካን ትንሽ ይሁን ትልቅ ሙሲባ ከአላህ ዘንድ አጅር ያስገኝልናል:: ከዚያ ዉድቀትና ችግር ለመውጣት በምናደርገው ጥረት ላይ ደግሞ አላህ ይረዳናል::

አላህ ያመጣብንን መከራዎች ወዶ መቀበል፣ በሙሲባዎች ያለ ማጉረምረም፣ ከችግር ጋር ማመሰገን፣ ከበሽታ ጋር ገለታ ለአላህ ማድረስም ሌላው ጂሃድ መሆኑን ልናውቅ ይገባል:: ይህን ማድረግ ከነፍስ ጋር መታገል ግድ ይላልና:: የበቃ ኢማን ያስፈልጋል:: ሁሉን ነገር ትቶ ለአላህ እጅ መስጠትን፣ አላህን ብቻ ማሰብን ግድ ይላል:: ባላዩት አላህ ማመን፣ ቃልኪዳኑን መተማመን፣ ነገን መጠበቅ፣ መታገስ፣ መፅናት፣ በአላህ ላይ አርግጠኛ መሆን፣ እሱ የወደደልንን መውደድ፣ ክፍፍሉን መቀበል፣ ሥራዉን ሁሉ ያለ ቅሬታ መቀበል ... ይህ ሁሉ ጂሃድ ነው::

ዱንያ ሁለመናዋ ጂሃድ ነው:: ችግሯም ድሎቷም ጂሃድ አለው፤ በፅኑ ለማመመንና በኢማን ለመቆየት ጂሃድ ይፈልጋል፤ በአላህ ላለመጠራጠርና ላለመከፈር ሳይቀር ጂሃድ ግድ ይላል:: ጂሃድ ማለት መታገል ነው:: **የአላህ ባሮች ሆይ ለመልካም ነገር ሁሉ ታገሉ:: ያለ ትግል የሚገኝ ጥሩ ነገር የለምና::** አላህ ሆይ በዲንህ ላይ አፅናን:: ጥሩ ታጋዮችም አድርገን::

እየረፍን ....

እምላኬ ሆይ! በዚህች ዓለም ቆይታዬ የወደድከልኝን ነገር ሁሉ ከልቤ የምወደው ለድርገኝ። ደካማ ባርያህ ነኝና አዝነትህ ሁሌም ሊይለየኝ። ታግዬ መቀየር በማልችለው ነገር ላይ ትዕግስትህን ስጠኝ። የሁልጊዜ ዓላማዬ መልካም ሰው መሆን ነወና መልካምነትን አጎናጽፈኝ። በእዝነትህ ቀናዒን መንገድ አመላከተኝ:: የዱንያ ቀናቴ ከባባድና ስልቹ ቢሆኑም እርጋታህን ለግሰኝ። አፈጣጠሬን ያሳመርከ አምላኬ ሆይ ባህሪዬንም አሳምርልኝ። ያ ረብ! ሁሌም የሠጠኸኝን ሕይወት ወድጄ በየቀኑ ከእንቅልፌ የምነቃ አድርገኝ።

****

ምድር ላይ ሲኖር የሰው ልጅ ሊደርስበት የሚችለው ትልቁ የስኬት ጣርያ የአላህ ሱ.ወ. ባርያ መሆን ነው። የአላህ ባርያ ከመሆን በላይ ዕድለኛለነት የለም:: ለርሱ የተዋረደ አገልጋይ ከመሆን በላይ ንግሥና የለም:: እሱን ማገልገል መቻል ከአላህ በኩል ለባርያው የተሠጠ ሽልማት ነው:: የተመረጠ ሰው ማለትም በአላህ የተመረጠው ነው:: ለአምላካችን አላህ ሱ.ዉ. ባርነታችንን የምንገልፀው እሱን በመታዘዝ፣ ለሱ በመተናነስ፣ ለሱ ሩኩዕ እና ሱጁድ በማድረግ፣ ሶላትና ሌሎች ዒባዳዎችን አጥብቆ በመያዝ ዉስጥ ነው:: ዝቅ ባልከ ቁጥር ከፍ ትላለህ:: በፈራኸው ቁጥር ከብር ታገኛለህ:: በወደቅከ ቁጥር መነሳትህ እርግጥ ነው:: አላህ ሆይ ይህን ዕድል ለኛ ስጠን:: ባሮችህ አድርገህ አዉለን፣ አሳድረን፣ አዝልቀን፣ አኑረን፣ ግደለን፣ ቀስቅሰንም።

***** ወዳጆቼ .. ይህች ዓለም ጫፏ ላይ ለመድረስ እሩቅ ትመስላለች እንጂ ቅርብ ናት:: ይኸው አንድ ቀን የኖርን ሳይመስለን ሀያ፣ አርባ፣ ስልሳ ዓመት ደረስን እኮ:: ትናንት በሰዎች ቶሎ ማርጀት ስንገረም የነበርን ሰዎች ዛሬ ላይ ሆነን ደግሞ ስለ ጡረታ ማሰብ ጀምረናል:: ዱንያ እንደ አንዲት ቀን ናት:: እንደ ፀሐይ ሁሉ ትወጣለች ትገባለች:: ሲነጋ ሰዎች የከበዳቸዉን ጨለማዉን መገፈፍ የተገላገሉ ይመስል እንዴት አደራችሁ ሰባሐል ኸይር ይባባላሉ:: ሰባኸል ኸይር ንጋትን፣ ተስፋን፣ ብሥራትን የቀኑን ብሩህነት ያመለክታል:: ዱንያም እንዲሁ ናት:: የጨለመ ይነጋል፣ እንደመሸ አይቀርም፤ የሞላ ወንዝም ያልፋል እንደሞላ አይዘወትርም::

ዱንያ ፀሐይ ናት:: ጊዜዋን ጠብቃ ትጠልቃለች:: ዕድሜያችንም እንደዚያው:: ማለዳ ረፋድ፣ ቀትር አመሻሽ አለው:: ምንም ችግር ጎብኝቶት እንደማያውቅ ሰው ፈገግ ካላላችሁ የዱንያ ጨለማ መቸም አይገፍላችሁም::

ምርጡን ምርጫህን ልንገርህ

ለኔ የምልህ ወዳጄ ... የኛና የዱንያ ነገር የተወሰነው ገና ድሮ መሆኑን ታውቃለህ ላይደለ! _ ለም ለናኖርን ያለነው ገና ከመወለዳችን በፊት የተግፈልንን ሕያውት ነው;; ስለዚህ ሁሌም በለንድ ባለመጠህ ነገር ከመነሳሳነሮህ በፊት ይሆንኑ አሰታውሰ:: ለናኖርን ያለነው አላህ የፃፈልንን ነገር ነው:: አየተጓገዝን ያለነዉም አላህ ባሰመረልን መንገድ ነው::

አንዳንዴ ምድር ላይ ኖረህ የሆነ አርከን ላይ ሰትደርስ መለሰ ብለህ ነገሮችን የምትቃኝበትን ፋታ ታገኛለህ:: ነገሮችንም እንደ አዲስ ትመረምራለህ:: ሕያውት ባሰብከው መንገድ ትታ ወዳላሰብከው መንገድና ማረፊያ ሰትወሰድህ ነገሮች እንዴት እንዲህ ሆኑ፣ እንዴት ከዚህ ደረሱ .. ትላለህ:: አንዳንዴም ትቆጫለህ፣ ባስ ሲልም ታዝናለህ::

ወዳጄ ... ሥራ ይሁን ትዳር፣ ሙያ፣ ትምህርት ይሁን ሌላ ነገር ... ያ በሕይወትህ አመለጠኝ ብለህ ሁሌ የምትብሰለሰልበት ነገር እኮ ምርጡ ምርጫህ ላይሆን ይችላል። ያ በተሳካልኝ ብለህ ሁሌ የምትቆጭበትና የምታዝንበት ነገር ቆንጆው ዕድልህ ላይሆን ይችላል እኮ:: ምንጊዜም ቢሆን ምርጡ ምርጫ አላህ የመረጠልህ ነው።

አዎ ምርጡ ምርጫህ አሁን ያለህበት ነገር ነው:: አሱንም አላህ ነው የመረጠልህ:: አላህ የመረጠልህ ነገር ቀድሞዉኑ ነበርና ዘመን ወደኋላ ቢመልስህ እንኳ አሁን ከመረጥከው ዉጭ ሌላ ነገር አትመርጥም። ምክንያቱም ጉዳዩ የአላህ ፈቃድ አለበት።

ስለሆነም ወዳጄዋ ... የሆነው ሁሉ ሊሆን የቻለው በአላህ ፈቃድ ነዉና ምንም ያመለጠህ ነገር እንደሌለ አወቅ። አትጠራጠር ትከከለኛ ቦታ ላይ ነው ያለኸው:: በመሆኑም ሰላለፈው ነገር አያሰብከ በሀሳብ ወደኋላ በመሄድ አትንገላታ፣ አትናደድ፣ አትወዛገብ፣ አትበሳጭ። ባለህበት ተረጋግተህ፣ አላህ የወደደልህን ወደህ፣ ተደስተህና አረከተህ ኑር።

አንዳንዴ ዉስጣዊ ሰላማችን ሲናጋና ያለንበትን የዛሬ ሁኔታችን ደስ ሳይለን ሲቀር ወደኋላ ሄደን በድሮ ዉሣኔዎቻችንና አካሄዳችን እንቆጫለን። ባለፈው እንበሣጫለን:: ይህ መሆን የለበትም። ያገኘኸው ነገር ላያመልጥህ የተፃፈ ነው። ያመለጠህ ደግሞ በፊቱኑ ላታገኘው የተወሰነ ነገር ነው። እና አርጋ አትበሰልሰል ወንድሜ። ተረጊ አህቴዋ። ሶባሐል ኸይር!!

ለአላህ የሆነው ይዘልቃል!

ታላቁ፣ ደጉና ዓሊሙ የአላህ ሰው ዐብዱላህ ኢብኑ አልሙባረክ ረሒመሁሏህ ኢማም ዳሩል ሂጅረህ ተብለው ስለሚታወቁት ስለ ኢማም ማሊክ ኢብኑ አነስ ረሒመሁሏህ ሲናገሩ " የማሊክ ዓይነት አላህ ከፍ ያደረገው ሰው አላየሁም፤ በርግጥ ብዙ ዖምም ሆነ ሶላትም ኖሮት አይደለም:: ብቻ በሱ እና በአላህ መካከል የሆነ ሚስጢር ያለ ይመስለኛል::" ይላሉ::

እኛም ደጉ ሰው ኢብኑል ሙባረክ የመሠከሩላቸው ኢማሙ ማሊክ ደግ ናቸው ብለን እናስባለን:: ደጋግ ሰዎች በርግጥም ሌሎች ሰዎች የማያውቋቸዉና የማይደርሱባቸው በነርሱ እና በአላህ መካከል ልዩ ያስቀመጡት ደግ ሥራ እና የመገናኛ መስመር አላቸው:: አላህ ዘንድ በድብቅ ያስቀምጣሉ፤ አርሱ ዘንድ ያስመጡት ደግ ሥራ እንደማይጠፋ ያውቃሉና ነው::

ኢማም ማሊክ ግዙፉን አል-ሙወጦእ የተሠኘዉን መጽሐፋቸዉን በማዘጋጀት ላይ እያሉ ሰዎች " ኢማም ሆይ! ሰው ሁሉ ስለ ሐዲሥ እየፃፈ ነው:: የሐዲሥ መፃሕፍት ብዙ ናቸው:: ያለው እኮ በቂ ነው፤ የርስዎ መጽሐፍ ምን ያደርጋል?::" አሏቸው::

ኢማም ማሊክም ሳያንገራግሩ "ለአላህ ከሆነ ይዘልቃል::" አሏቸው::

የአላህ ሰዎች እንዲህ ናቸው:: አንድን መልካም ሥራ ሲጀምሩም ሆነ ሲቀጥሉ ልቦናቸዉን ይፈትሻሉ፤ ዓላማቸዉን ይመረምራሉ፤ ሀሳባቸዉን ይከልሳሉ:: እንደዉም ለአላህ ካልሆነ አይጀምሩትም፤ አይቀጥሉትም፤ አይጨርሱትምም:: በርግጥ ኪታባቸው ምእተ ዓመታትን ዘልቆ ዛሬ በእጃችን ላይ ይገኛል:: አርሣቸዉም ከአራቱ የኢስላም እውቅ የመዝሀብ ኢማሞች መካከል አንዱ ሆነው ሥማቸው ዛሬም ድረስ በዓለም ማዕዘናት ይወሳል::

"ለአላህ ከሆነ ይዘልቃል::" ኢማሙ ይህችን ቃል ሲናገሩ ከዉስጥ ሀሳባቸው ጋር ሙግት ዉስጥ የገቡ ይመስላሉ:: ሥራዬ ዕድሜም ሆነ ዘላቂነት የሚኖረው ከአላህ ጋር ባለኝ የትስስር ልክ ነው ማለታቸው ነው:: እኔ በርግጥ እሠራለሁ፤ ከኔ የሚጠበቀው አላህን አስቤ መሥራት ብቻ ነው:: ልቤን የሚያየው እና ዓላማዬን የሚውቀው አላህ ሥራዬ ለርሱ መሆኑን ካወቀና ከወደደ ያዘልቀዋል፤ መድረስ ላለበት ያደርሰዋል ማለታቸው ነው:: አላህም "ሥሩ ሥራችሁን አያለሁ" ብሎናል::